324

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር / Ref. No 3.3-0/56/10
ቀን / Date 10 ታህሳስ 2010

የጉምሩክ ስነ ስርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች
__በያሉበት__

**ጉዳዩ፡- የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ታህሳስ 05 ቀን 2010 በቁጥር ገ/ኢ/1/2/222 በፃፈልን ደብዳቤ ለንግድ ማይውሉ ወደ አገር የሚገቡ የግል መገልገያ እቃዎችን በሚመለከት መመሪያ ቁጥር 51/2010 አውጥቶ በማጽደቅ ተፈፃሚ እንዲደረግ አሳውቆናል፡፡ ስለሆነም ይህንኑ የግል መገልገያ እቃዎች መመሪያ ከነሰንጠረዡ 32 ገጽ የላክንላቹሁ መሆናችንን እየገለጽን ተገቢውን መረጃ በመያዝና ከመመሪያው አኳያ ህጋዊ ቁጥጥር በማድረግ ተፈፃሚ እንድታደርጉ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ
የጉምሩክ ጉዳይ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

**ግልባጭ፤**

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለህግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ጉዳይ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ሥነ ሥርአት ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
- ለድህረ እቃ አወጣጥ ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት

__ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን__

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን !!

ስልክ ቁ / Tel.. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet .et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ -ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

ገቢ 1467
10-04-10

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
# The Federal Democratic Republic of Ethiopia
# Ministry of Finance and Economic Cooperation

ቁጥር Ref.No. 7/ሂ/1/2/222
ቀን Date 5/4/2010

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

<u>አዲስ አበባ</u>

ለንግድ የማይውሉ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የግል መገልገያ ዕቃዎችን ቀረጥና ታክስ አወሳሰን በሚመለከት ወጥ የሆነ የታሪፍ መጣኔ ስርዓት ተፈፃሚ እንዲሆን በጉምሩክ አዋጅ የተደነገገ ሲሆን፣ ይህን አፈፃፀም የሚመራ መመሪያ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እንዲያወጣ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 2(24) እና 2(52) ስልጣን ተሰጥቶታል።

ስለዚህ ይህንኑ አፈፃፀም የሚወስነውን መመሪያ ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆን በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሣስባለን።

ከሠላምታ ጋር

አብረሃም ተከስተ (ዶ/ር)
ሚኒስትር

Letter/H/E.T

ስልክ Tel 251-11-155 24 00, 22 66 98
251-11-155 00 81, 83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
ፋክስ Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa- Ethiopia

# የግል መገልገያ ዕቃዎች መመሪያ ቁጥር 51/2010

## የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር

የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2

Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2

Der/Hb/TA

በአየር መንገድም ሆነ በየብስ ከውጭ አገር የሚመጡ መንገደኞች፣ ተመላሽ ኢትዮጵያዊያን እና በተለያዩ ሙያዎች ኢትዮጵያ ዉስጥ ለማገልገል በህጋዊ መንገድ ተቀጥረዉ የሚመጡ ትዉልደ ኢትዮጵያዊያን ወይም የዉጭ አገር ዜጎች፣ መንግስት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ መሰረት የሚመጡ ኢትዮጵያዊያን ወይም ትውልደ አትዮጵያዊያን ወይም የውጭ አገር ዜጎች የሚስገቧቸው እና የሚስወጧቸው እንዲሁም በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ አገር ቆይተው ጠቅለው የሚመለሱ ኢትዮጵያዊያን ወይም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሚያስገቧቸውን ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ እቃዎች የቀረጥና ታክስ አከፋፈል በሚመለከት ወጥ የሆነ አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

ለንግድ የማይውሉ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የግል መገልገያ ዕቃዎችን ቀረጥና ታክስ አወሳሰን በሚመለከት ወጥ የሆነ የታሪፍ መጣኔ ስርዓት ተፈጻሚ እንደሚሆን በጉምሩክ አዋጁ የተደነገገ በመሆኑ፣

በአየር ትራንስፖርት ለሚጓጓዙ መንገደኞች የሚሰጠዉን የጉምሩክ አገልግሎት ማሰለጥ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 2(24)፣2 (52) እና 33(2) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎችን ዝርዝር ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 51/2010 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1) **"ለንግድ የማይውል ዕቃ"** ማለት ጠቅላላ ዋጋው ወይም ብዛቱ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ ከተወሰነው መጠን የማይበልጥ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልበት እና ለባለቤቱ ወይም ለባለይዞታው ወይም ለቤተሰቡ የግል መገልገያ

ወይም ፍጆታ የሚውል በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተጠቀሰ ባለመብት ይዞት ወይም ከባለመብቱ ተለይቶ የሚመጣ ዕቃ ነው።

2) **"የግል መገልገያ ዕቃ"** ማለት ጠቅላላ ዋጋው ወይም ብዛቱ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ ከተወሰነው መጠን የማይበልጥ ቀረጥና ታክስ የማይከፈልበት እና ለባለቤቱ ወይም ለባለይዞታው ወይም ለቤተሰቡ የግል መገልገያ ወይም ፍጆታ የሚውል በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተጠቀሰ ባለመብት ይዞት ወይም ከባለመብቱ ተለይቶ የሚመጣ ዕቃ ነው። ፡፡

3) **"መንገደኛ"** ማለት ማንኛውም በየብስ በኢትዮጵያ መግቢያና መውጫ በሮች ወይም በዓለም አቀፍ የአየር ማረፊያዎች በኩል ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ወይም ከኢትዮጵያ የሚወጣ ሰው ሲሆን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4(2) የተጠቀሱትን ባለመብቶች አይጨምርም።

4) **"ተመላሽ ኢትዮጵያዊ"** ማለት በህጋዊ መንገድ ወይም ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ከኢትዮጵያ ወጥቶ በሚኖርበት አገር የስራና የመኖሪያ ፈቃድ አግኝቶ ሲኖር የነበረ ሆኖ ጠቅሎ የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ነው።

5) **"በተለያዩ ሙያዎች ለማገልገል የሚመጣ"** ማለት ኢትዮጵያ ዉስጥ በሙያዉ በተለያዩ መንግስታዊ መ/ቤቶች፣ መንግስታዊ የልማት ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ዓለምአቀፍ፣አህጉርአቀፍ ወይም አገር አቀፍ ድርጅቶች፣ ህጋዊ ማህበራት፣ የግል ድርጅቶች፣ የመንግስትና የግል የጋራ ድርጅቶች ውስጥ ለማገልገል በህጋዊ መንገድ ተቀጥሮ ወይም በሌላ ህጋዊ ስምምነት ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የዉጭ አገር ዜጋ ነው ፡፡

6) **"ወጥ የሆነ የታሪፍ መጣኔ"** ማለት ዕቃዎች ከመደበኛው የታሪፍ መጣኔ በተለየ ሁኔታ የሚስተናገዱበት ልዩ የታሪፍ መጣኔ ሆኖ በባህሪያቸውም ሆነ በሌላ ሁኔታ ተቀራራቢነት ያላቸውን ዕቃዎች በመለየት ለእያንዳንዱ ዕቃ ከጠቅላላ ቀረጥና ታክስ በመነሳት አማካይ የታሪፍ መጣኔ በማስላት የሚገኝ ልዩ የታሪፍ መጣኔ ነው።

7) **"ከስደት ተመላሽ"** ማለት በተለያዩ ምክንያቶች ከኢትዮጵያ ወጥቶ በስደት የኖረና በራሱ ፈቃድ ወይም በመንግስት ስምምነት ያለ ፓስፖርት ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስ ወይም በተቀባዩ አገር የጥገኝነት ጥያቄው ተቀባይነት ያላገኘ እና በራሱ ፈቃድ በሊሴ ፓሴ ወይም በነበረበት አገር መንግስት ተገዶ ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡

8) **"ትምህርት"** ማለት በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ካሪኩለም የሚታቀፍ ወይም የትምህርት ሚኒስቴር የሚቀበለው የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ከመጀመሪያ ዲግሪ በላይ የሆነ ትምህርት ነው፡፡

9) **"ባለስልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ነዉ፡፡

10) **"ሚኒስቴር"** ማለት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ነው፡፡

11) **"አዋጅ"** ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ነው፡፡

12) በዚህ መመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቃላትና ሀረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ፡-

ማንኛዉም መንገደኛ፣ ተመላሽ ኢትዮጵያዊ ፣ ከስደተኛ ተመላሽ እና በተለያዩ ሙያዎች ኢትዮጵያ ዉስጥ ለማገልገል በህጋዊ መንገድ ተቀጥሮ ወይም በሌላ ህጋዊ ስምምነት ኢትዮጵያ ዉስጥ ለማገልገል በአየር ወይም በየብስ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ወይም ከኢትዮጵያ የሚወጣ ኢትዮጵያዊ ወይም ትዉልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የዉጭ አገር ዜጋ፣ መንግስት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ መሰረት የሚመጣ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ አትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ዜጋ ፣ ማንኛውም ባለሀብት እንዲሁም አንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ በግል ስራ፣ በቅጥር ወይም በትምህርት ውጭ አገር የቆየ ኢትዮጵያዊ ወደ አገር ውስጥ በሚያስገቧቸው ወይም ከአገር በሚያስወጧቸው የግል መገልገያ ዕቃዎች እና ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የግል መገልገያ እቃዎች እና ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ እቃዎች

4. **የግል መገልገያ እቃ**

1) ማንኛውም መንገደኛ፡-

ሀ. በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ሐ" ላይ የግል መገልገያ ዕቃ ተብለው በአይነት፣በመጠንና በብዛት ተለይተው የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፍል ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል።

ለ. በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "መ" ላይ ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃ ተብለው በአይነት፣በመጠንና በብዛት ተለይተው የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ከፍሎ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል።

ሐ. በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ሐ" ላይ ወጪ የግል መገልገያ ዕቃዎች ተብለው በአይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይተው የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ወደ ውጭ አገር ይዞ መውጣት ይችላል።

2) ተመላሽ ኢትዮጵያዊ ፣ በተለያዩ ሙያዎች ኢትዮጵያ ዉስጥ ለማገልገል በህጋዊ መንገድ ተቀጥሮ ወይም በሌላ ህጋዊ ስምምነት ኢትዮጵያ ዉስጥ ለማገልገል የሚመጣ ትዉልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የዉጭ አገር ዜጋ፣ መንግስት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ የሚመጣ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ አትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ዜጋ፣ ማንኛውም ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ያደረገ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ ባለሀብት እና አንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ በግል ስራ፣ በቅጥር ወይም በትምህርት ውጭ አገር የቆየ ኢትዮጵያዊ፡-

ሀ. በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ሠ" ላይ የግል መገልገያ ዕቃ ተብለው በአይነት፣በመጠንና በብዛት ተለይተው የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፍል ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል።

ለ. በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ረ" ላይ ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃ ተብለው በአይነት፣በመጠንና በብዛት ተለይተው የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ከፍሎ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለማስረጃ አያያዝና አቀራረብ

5. **መረጃ ስለመያዝ**

ለዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 እና 7 አፈጻጸም ባለስልጣኑ የስጋት ስራ አመራርን መሠረት በማድረግ የተሟላ መረጃ በቋሚነት መያዝ አለበት፡፡

6. **ስለማስረጃ አቀራረብ**

1) **ተመላሽ ኢትዮጵያዊ፡-**

ሀ/ በውጭ አገር የቆየበትን ጊዜ እና ጠቅሎ ወደ ኢትዮጵያ መመለሱን የሚገልጽ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ (Authenticated) የመሸኛ ደብዳቤ ከነበረበት አገር ካለው ወይም የነበረበትን ሀገር ጭምር ከሚያገለግለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም ሚሲዮን ማቅረብ አለበት፡፡

ለ/ የኢትዮጵያ ሚሲዮን ከሌለበት አገር የሚመጣ ከሆነ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የመኖሪያ ፈቃዱን እና የሥራ ውሉን ሳያሰርዝ የመጣ መሆኑን በማጣራት በፓስፖርቱ ላይ በተለጠፈው ስቲከር ላይ ተሰርዟል (void) የሚል ማህተም በማድረግ የሚሰጠውን የመሸኛ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2) **ከስደት ተመላሽ፡-**

ሀ/ ከስደት ተመላሽ በስደት በቆየበት አገር ካለው ወይም በስደት የቆየበትን ሀገር ጭምር ከሚያገለግለው የአትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም

ሚሲዮን የተሰጠውን መሸኛ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል አረጋግጦ ማቅረብ አለበት፡፡

ለ/ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም ሚሲዮን ከሌለበት አገር የሚመጣ ከሆነ ከደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን ከስደት ተመላሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡፡

ሐ/ በስደተኛነት ቆይቶ በላኪው ሀገር እና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት ወደ ኢትዮጵያ የሚመለስ ከስደት ተመላሽ ከደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ከስደት ተመላሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡፡

3) <u>ባለሀብት</u>

ማንኛውም ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ያደረገ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ ባለሀብት፣ ባለሃብት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚመለከተው የኢንቨስትመንት ኮሚሽን/ቢሮ ማቅረብ አለበት፡፡

4) <u>አግባብ ካለው የመንግስት መ/ቤት ወይም ተቋም ጋር በተደረገ ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ለማገልገል የሚመጣ ባለሙያ</u>፡-

አግባብ ካለው የመንግስት መ/ቤት ወይም ተቋም ጋር በተደረገ ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ለማገልገል የሚመጣ የውጭ አገር ነዋሪ ኢትዮጵያዊ፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ እና የውጭ አገር ዜጋ ባለሙያ ስምምነቱን ባደረገው የመንግስት መ/ቤት ወይም ተቋም የበላይ ኃላፊ የተፈረመ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡፡

5) <u>መንግስት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ የሚመጣ</u>

መንግስት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ መሰረት በኢትዮጵያ ለማገልገል የሚመጣ የውጭ አገር ነዋሪ ኢትዮጵያዊ፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ እና የውጭ አገር ዜጋ ባለሙያ በጥሪው መሰረት ኢትዮጵያን ለማገልገል መምጣቱን የሚያስረዳ ከነበረበት አገር ካለው ወይም የነበረበትን ሀገር ጭምር ከሚያገለግለው

የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም ሚሲዮን የተሰጠ እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ (Authenticated) ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡፡

6) <u>በግል ሥራ ፣ በቅጥር ወይም በትምህርት ቆይቶ የሚመጣ</u>

በግል ስራ፣ በቅጥር ወይም በትምህርት ውጭ ሀገር ቆይቶ የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ከመጣበት አገር ካለው ወይም የመጣበትን ሀገር ጭምር ከሚያገለግለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም ሚሲዮን የተሰጠ በዚሁ ሀገር ውስጥ በግል ሥራ፣ በቅጥር ወይም በትምህርት የቆየ መሆኑን የሚያስረዳ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፡፡

## ክፍል አራት
## ወጥ የታሪፍ መጣኔ አፈፃፀም

### 7. ወጥ የሆነ የታሪፍ መጣኔ አወሳሰን

1) በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "መ" እና "ረ" መሰረት የሚገቡ ለንግድ የማይወሉ የግል መገልገያ ዕቃዎች ወጥ በሆነ የታሪፍ መጣኔ መሠረት ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው ወደ አገር ውስጥ ይገባሉ፡፡

2) ለንግድ የማይውሉ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የግል መገልገያ ዕቃዎች የቀረጥ መጣኔ በጉምሩክ ታሪፍ ምዕራፍ 98 መሠረት ይወሰናል፡፡

3) ባለስልጣኑ ከአጠቃላይ የዋጋ አተማመን መርህ ጋር በማጣጣም ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎችን ዝርዝር የመነሻ ዋጋ ያዘጋጃል፡፡

### 8. ወጥ በሆነ የታሪፍ መጣኔ የማይስተናገዱ ዕቃዎች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ዕቃዎች ወጥ በሆነ የታሪፍ መጣኔ ሊስተናገዱ አይችሉም፡፡

1) ባለመብቱ ለራሱ እና ለቤተሰቡ ጥቅም ሊያውለው ከሚችለው መጠን በላይ በተደጋጋሚ የሚያመጣቸው በስጋት ስራ አመራር ክትትል የሚያዙ ዕቃዎች፣
2) ለንግድ ሊውሉ የሚችሉ ዕቃዎች፣
3) ለንግድ የማይውሉ ተብሎ በሠንጠረዡ ከተዘረዘረው መጠን ያለፉ ዕቃዎች፣

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

9. **ገደብ**

1) በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ሠ" እና "ረ" የተመለከተ ማንኛውም ባለመብት የሚያስገባውን ዕቃዎች በሙሉ በአንድ ሰነድ አጠቃሎ ወደ ኢትዮጵያ በገባ በስድስት ወር ጊዜ ዉስጥ ማስገባት አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተ ባለመብት የግል መገልገያ ዕቃዎቹን በአየር መንገድ እና በየብስ አንድ ጊዜ፣ ሆኖም ከሁለቱ የማስጫኛ ዘዴዎች በአንዱ ብቻ መጠቀም ከፈለገ በየብስ ወይም በአየር መንገድ ሁለት ጊዜ ብቻ ማስገባት አለበት፡፡ ሆኖም በዚህ መመሪያ በተፈቀደው መብት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

10. **በሠንጠረዥ ውስጥ ያልተካተቱት ዕቃዎች የሚስተናገዱበት አግባብ**

1) በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ ውስጥ ያልተካተቱ ለግል መገልገያነት የሚውሉ ወይም ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎች ሲመጡ በልዩ ሁኔታ በባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ወይም እርሱ በሚወክለው ስራ ኃላፊ ውሳኔ ይሰጥበቸዋል፡፡

2) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በልዩ ሁኔታ የተስተናገዱ ዕቃዎችን መግለጫ እና የዋጋ ዝርዝር የያዘ ሪፖርት በየጊዜው ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

11. **ስለ ዕቃ አፈታተሽ አግባብ**

1) ባለስልጣኑ በኢንተለጀንስ የሚያደርገው ክትትል እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ጉዞ ወይም ጭነት በአውሮፕላን በሚመጣ የመንገደኞች ሻንጣ ወይም የመንገደኞች ዕቃ ላይ 3% ብቻ በመውሰድ በስጋት ስራ አመራር መሰረት የጉምሩክ ፍተሻ ይደረጋል፡፡ ባለስልጣኑ ከብሔራዊ የአየር ትራንስፖርት ፋሲሊቴሽን ኮሚቴ ጋር በመመካከር ዝርዝር አፈፃፀሙ የሚመራበት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በተደነገገዉ መቶኛ ስርዓት ተወስደው የሚፈተሹ ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎች በዚህ መመሪያ በክፍል አራት እና ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ መሰረት ቀረጥና ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀው የስጋት ሥራ አመራር የመንገደኞች ዕቃ ፍተሻ ሥርዓት በሌሎች የማጓጓዛ ዘዴዎች በሚመጡ የመንገደኞች ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

4) ማንኛውም ባለመብት ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ሰንጠረዥ ከተፈቀደው መጠን በላይ ዕቃ ያመጣ እንደሆነ የዕቃውን ቀረጥና ታክስ በእጥፍ ይከፍላል፡፡ ሆኖም ቀረጥና ታክሱን መክፈል ያልቻለ እንደሆነ በትርፍነት ያመጣው ዕቃ ውርስ ተደርጎ ለመንግስት ገቢ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጊቱ በተደጋጋሚ የተፈፀመ እንደሆነ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሰረት ተጠያቂ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

5) ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "መንገደኛ" በአንቀጽ 4(2) የተጠቀሱትን ባለመብቶች ይጨምራል፡፡

13 <u>የተሻረ መመሪያ ወይም አሰራር</u>

1) ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ አሰራርና ልማድ በዚህ መመሪያ ላይ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም ይህ መመሪያ በሌላ ሕግ መሰረት የተፈቀደን የግል መገልገያ ዕቃዎች የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት አያስቀርም፡፡

## 14. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከታኅሳስ 6 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ___________ቀን 2010 ዓ.ም

ዶ/ር አብርሃም ተከስተ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር
ሚኒስትር

## ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎች ዝርዝር

| | | | ለመንገደኞች | | ለተመላሽ ኢትዮጵያዊያን፣በተለያዩ ሙያዎች ኢትዮጵያ ዉስጥ ለማገልገል በህጋዊ መንገድ ተቀጥረዉ ወይም በሌላ ህጋዊ ስምምነት ወደ ኢትዮጵያ ውስጥ ለማገልገል የሚመጡ ትዉልደ ኢትዮጵያዊያን ወይም የዉጭ አገር ዜጎች | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ | |
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | |
| | ገቢ የግል መገልገያ ዕቃዎች ዝርዝር | | | | | | |
| | 1. ኤሌክትሮኒክስ | | | | | | |
| 1 | ማንኛውም ቴሌቪዥን የኢንች ገደብ ሳይደረግበት ከነአክሰሰሪው | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 2 | ቴሌቪዥን ራክ ወይም የቴሌቭዥን ስታንድ | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| ተ.ቁ | 2. የጽሕፈት ህትመትና ኮፒ አገልግሎት ዕቃዎች | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | |
| 1 | Computer (ማንኛውም አይነት) | ሴት | | 1 | 2 | 2 | |
| 2 | LAPTOP(ማንኛውም አይነት) | በቁጥር | 1 | 2 | 2 | 3 | |
| 3 | Computer parts & accessories | ሴት | 1 | 2 | 2 | 3 | |
| 4 | palmtop/ Ipad/ Tablet | በቁጥር | 1 | 2 | 2 | 3 | |
| 5 | Hard disk (external) | በቁጥር | 2 | 4 | 4 | 4 | |
| 6 | Normal Printer | በቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| 7 | Ipod/ Mp player | በቁጥር | 2 | 2 | 4 | 5 | |
| 8 | Flash Disk | በቁጥር | 5 | 10 | 10 | 10 | |
| 9 | የፕሪንተር ቀለም | በቁጥር | | 10 | 4 | 10 | |

Ethiopian Revenues and Customs Autho... Records & Documentation No. 2

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | |
| ተ.ቁ | 5. የሸክላ ዲስክ ማጫዎቻ | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | |
| 1 | Home Theater with DVD and stand | ሴት | | 1 | 1 | 1 | |
| 2 | Deck with Receiver | ሴት | | 1 | 1 | 1 | |
| 3 | ሬዲዮ/ broadcast reciver | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 2 | |
| 4 | ቴፕ እስከ 2 ካሴት ማጫወቻ | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 5 | የሆም ሲኒማ ሲስተም ስፒከር | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| 6 | የቴፕ ስፒከር | ሴት | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 7 | የኮምፒዉተር ስፒከር | ሴት | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 8 | ድምፅ ማጉያ(Micro phone) | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| 9 | የሙዚቃ መሣርያ ስታንድ | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| 10 | የቴፕ ካሴት/ሲዲ/ቪዲዮ/ የሸክላ ዲስክ የተለያዩ የተቀረጸበት ያገለገለ | ቁጥር | ነጻ | ነጻ | ነጻ | ነጻ | |

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት |
| ተ.ቁ | 6.የመገናኛ መሣርያዎች | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት |
| 1 | የስልክ ቀፎ ባለ መሥመር የማይንቀሳቀስ | ቁጥር | 2 | 3 | 5 | 5 |
| 2 | የስልክ ቀፎ ባለ መሥመር ተንቀሳቃሽ | ቁጥር | 2 | 3 | 5 | 5 |
| 3 | የስልክ መቀበያ | ቁጥር | 2 | 3 | 5 | 5 |
| 4 | የሞባይል ቀፎ | ቁጥር | 2 | 3 | 4 | 10 |
| 5 | የሞባይል ቀፎ ከቨር (ኬዝ) | ቁጥር | 3 | 3 | 4 | 10 |
| 6 | Receiver | ቁጥር | 1 | 2 | 1 | 2 |
| 7 | LNB | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 8 | Dish | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 |
| 9 | Cable 1 ጥቅል(200ሜትር) | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 |
| ተ.ቁ | 7. የማዕድ ቤት ዕቃዎች | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት |
| 1 | ባለ1 ወይም 2 ወይም ከ2 በላይ መጣጃ ምድጃ በኤሌክትሪክ ወይም በጋዝ የሚሰራ | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 2 | ቶስተር(የዳቦ ማሞቂያ) | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 |
| 3 | የዳቦ ምጣድ ለቤት አገልግሎት | ቁጥር | | 1 | 1 | 2 |
| 4 | ጀግ መሣይ የውሃ ማሞቂያ | ቁጥር | 1 | 2 | 1 | 2 |

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት |
| 26 | ብረት ድስት | ሴት | 1 | 2 | 3 | 5 |
| 27 | ማኑዋል ፓስታ መስሪያ | በቁጥር | 1 | 2 | 2 | 3 |
| 28 | የፓስታ ማጥለያ | በቁጥር | 2 | 2 | 2 | 2 |
| 29 | ፔርሙስ | በቁጥር | 1 | 2 | 5 | 5 |
| 30 | ረከቦት | በቁጥር | 1 | 1 | 2 | 3 |
| 31 | የቡና ስኒ | ደርዘን | 1 | 1 | 4 | 4 |
| 32 | ሰሀን | ደርዘን | 1 | 1 | 4 | 4 |
| 33 | ጉድጎዳ ሳህን | ደርዘን | 1 | 1 | 4 | 4 |
| 34 | የሻይ ብርጭቆ | በደርዘን | 1 | 1 | 4 | 4 |
| 35 | የውስኪ ብርጭቆ | በደርዘን | 1 | 1 | 4 | 4 |
| 36 | የወይን ብርጭቆ | በደርዘን | 1 | 1 | 4 | 4 |
| 37 | የውሃ ብርጭቆ | በደርዘን | 1 | 1 | 4 | 4 |
| 38 | ጭልፋ | በደርዘን | 1 | 1 | 4 | 4 |
| 39 | ትሪ | በቁጥር | 2 | 3 | 10 | 10 |
| 40 | ማንቆርቆሪያ | በቁጥር | 1 | 3 | 10 | 10 |
| 41 | ማንቆርቆሪያ መሰል የእጅ ማስታጠቢያ | በቁጥር | 1 | 3 | 10 | 10 |
| 42 | ከብረት የተሠራ ወንፊት | በቁጥር | 1 | 3 | 10 | 10 |
| 43 | ከብረት የተሠራ ማጥለያ | በቁጥር | 1 | 3 | 10 | 10 |
| 44 | ቤርጋሞር የቡና ረከቦት የሚያርፍበት | በቁጥር | | 3 | 10 | 10 |
| 45 | ፕላስቲክ የመጠጥ ውሃ ማቅረቢያ | በቁጥር | 5 | 5 | 10 | 10 |
| 46 | አሉሙኒየም ፎይል(aiuminum folil) | ጥቅል | 2 | 2 | 2 | 4 |
| 47 | እጣን | ኪሎ | 2 | 2 | 4 | 6 |
| 48 | በሶኬት የሚሰራ ትንንሽ የእጣን ማጨሻ | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 2 |
| 49 | መስታወት መሰል የእጣን መያዥ | በቁጥር | 1 | 3 | 2 | 3 |
| 50 | ትልቅ የእጣን ማጨሻ | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 51 | የስጋ መጥበሻ(GRILL) አነስተኛ | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 2 |
| 52 | የጋዝ ሲሊንደር | በቁጥር | | 2 | 2 | 4 |

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት |
| ተ.ቁ | 8. የባኞ ቤት ዕቃዎች | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት |
| 1 | ግድግዳ ላይ ተለጣፊ የውሃ ማሞቂያ (Boiler) | ቁጥር | | 2 | 2 | 3 |
| 2 | ኢንስታንት ውሀ ማሞቅያ ተለጣፊ | ቁጥር | 1 | 2 | 4 | 4 |
| 3 | የባኞ ገንዳ | በቁጥር | | 1 | 1 | 1 |
| 4 | የመፀዳጃ መቀመጫ ገንዳ | በቁጥር | | 1 | 1 | 1 |
| 5 | ጃኩዚ እና ስቲም | በቁጥር | | 1 | 1 | 2 |
| ተ.ቁ | 9. የፅዳትና የንጽህና መስጫ ዕቃዎች | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት |
| 1 | የልብስ ማጠቢያ ማሽን የማጠብ ችሎታው | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 |
| 2 | ቫኪዩም ክሊነር(Vaccum Cleaner) home | ቁጥር | | 2 | 2 | 3 |
| 3 | የልብስ መተኮሻ ካዉያ | ቁጥር | 1 | 2 | 2 | 2 |
| 4 | ለቤት ውስጥ አገልግሎት የልብስ መተኮሻ እስቲም ካውያ | ቁጥር | 1 | 2 | 2 | 3 |
| 5 | የልብስ መተኮሻ ጠረጴዛ | ቁጥር | | 2 | 2 | 2 |
| 6 | የልብስ ማድረቂያ ማሽንከ12 ኪ.ግ ያልበለጠ | በቁጥር | | 1 | 1 | 1 |
| 7 | የልብስ ማስጫ ብረት | በቁጥር | | 4 | 8 | 8 |

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት |
| 8 | የልብስ ማስጫ ገመድ | በሜትር | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 9 | የልብስ መቆንጠጫ | ደርዘን | 2 | 10 | 10 | 10 |
| 10 | የዱቄት ሳሙና | ኪ.ሎ | 10 | 10 | 10 | 20 |
| 11 | የገላ ሳሙና | ደርዘን | 2 | 4 | 4 | 6 |
| 12 | የልብስ ሳሙና | በደርዘን | 2 | 4 | 2 | 4 |
| 13 | ፈሳሽ ሳሙና | ሊትር | 10 | 10 | 10 | 10 |
| 14 | ማንጫ(በረኪና) | ሊትር | 5 | 10 | 10 | 10 |
| 15 | የጥፍር መቁረጫ | ደርዘን | 1 | 2 | 2 | 4 |
| 16 | የጥፍር መሞረጃ | ደርዘን | 1 | 1 | 2 | 2 |
| ተ.ቁ | 10. የህፃናት መጫወቻና መገልገያ ዕቃዎች | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት |
| 1 | በኤሌክትሪክ የሚሠራ ትልቁ የህፃናት መኪና/ሞተር ሳይክል | ቁጥር | | 2 | 3 | 4 |
| 2 | በባትሪ የሚሰራ ትልቁ የህፃናት መኪና | ቁጥር | | 2 | 1 | 2 |
| 3 | በሰው ወይም በመካኒካል የሚሠራ ትልቁ የህፃናት መኪና | ቁጥር | | 2 | 1 | 2 |
| 4 | ትንንሽ የህፃናት መኪና | ቁጥር | 2 | 6 | 4 | 6 |
| 5 | ማንኛውም ፕሌይ ስቴሽን(play Station) | ሴት | 1 | 4 | 4 | 4 |
| 6 | የህጻናት ልጅ ጋሪ | በቁጥር | 1 | 4 | 4 | 4 |
| 7 | አሻንጉሊት ትንንሽ | በቁጥር | 4 | 12 | 6 | 12 |
| 8 | አሻንጉሊት ትልልቁ | በቁጥር | 3 | 6 | 6 | 9 |
| 9 | የልጆች መጫወቻ (simulator) | በቁጥር | 4 | 4 | 4 | 6 |
| 10 | በአየር የሚነፋ ባውንሰር | በቁጥር | 4 | 4 | 4 | 4 |

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | |
| ተ/ቁ | 11. የፀጉር ቤት ዕቃዎችና ተዛማጅ መጠቀሚያዎች | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | |
| 1 | የፀጉር ቤት ወንበር | ቁጥር | | 1 | 1 | 2 | |
| 2 | የፀጉር ቤት መታጠቢያ ገንዳ | ቁጥር | | 2 | 2 | 2 | |
| 3 | የፀጉር ስታይሰር | ቁጥር | | 2 | 4 | 6 | |
| 4 | ፓይስትራ/ከርለር | ቁጥር | | 2 | 5 | 6 | |
| 5 | የፀጉር ጌጥ | ደርዘን | 2 | 6 | 4 | 6 | |
| 6 | የሰው ፀጉር (Human Hair) | እሽግ | 1 | 2 | 4 | 4 | |
| 7 | ዊግ (አርተፊሻል ፀጉር) | እሽግ | 1 | 2 | 4 | 6 | |
| 8 | ሂና | ደርዘን | 1 | 2 | 2 | 2 | |
| 9 | የፀጉር ቀለም | እሽግ | 1 | 6 | 6 | 12 | |
| 10 | ፐርም | ቁጥር | 2 | 6 | 4 | 6 | |
| 11 | ጄል | ቁጥር | 2 | 6 | 4 | 6 | |
| 12 | የፀጉር ካስክ | በቁጥር | | 1 | 1 | 2 | |

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | |
| 9 | የመብራት ማብሪያና ማጥፊያ | ቁጥር | 2 | 6 | 12 | 12 | |
| 10 | የሞባይል ቻርጀር | ቁጥር | 2 | 4 | 4 | 8 | |
| 11 | የላፕቶፕ ቻርጀር | ቁጥር | 1 | 4 | 4 | 8 | |
| 12 | የፎቶ ካሜራ ቻርጀር | ቁጥር | 2 | 4 | 4 | 8 | |
| ተ.ቁ | 14 የሳሎንና የመኝታ ቤት ዕቃዎች | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | |
| 1 | ቁም ሳጥን (በማንኛውም ማቴሪያል የተሰራ) | ቁጥር | | 2 | 2 | 4 | |
| 2 | መደርደሪያ(በማንኛውም ማቴሪያል የተሰራ) | ቁጥር | | 2 | 2 | 4 | |
| 3 | ኮንትሮል ቡፌ | ቁጥር | | 2 | 2 | 4 | |
| 4 | ኮመዲኖ | ቁጥር | | 2 | 2 | 4 | |
| 5 | የአዋቂ አልጋ ከነ ኮመዲኖው (በማንኛውም ማቴርያል የተሰራ) | ቁጥር | | 1 | 1 | 2 | |
| 6 | የልጅ አልጋ ከነፍራሹ ስፋቱ እስከ 1 ሜትር | ቁጥር | 1 | 1 | 4 | 2 | |
| 7 | የህጻን ልጅ አልጋ ከነፍራሹ | ቁጥር | 1 | 1 | 4 | 2 | |
| 8 | ድሬስንግ ቴብል | ቁጥር | | 1 | 2 | 2 | |
| 9 | የሳሎን ጠረጴዛ | ቁጥር | | 1 | 2 | 2 | |
| 10 | የቤት ውስጥ ወንበር | ቁጥር | | 12 | 12 | 12 | |
| 11 | አረቢያን መጀሊስ (መቀመጫውና የኋላ | በሴት | | 1 | 2 | 2 | |
| 12 | ሶፋ | ሴት | | 1 | 1 | 2 | |
| 13 | ምንጣፍ | ካሬ | | 40 | 40 | 60 | |

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት |
| 14 | እያንዳንዱ ግማሽ ሜትር በ1 ሜትር የሆነ መስገጃ ምንጣፍ | ቁጥር | 2 | 6 | 4 | 24 |
| 15 | የግድግዳ ሠአት | ቁጥር | 1 | 2 | 2 | 4 |
| 16 | መጋረጃ ከነ አክሰሰሪው(የተዘጋጀ) | በሴት | | 3 | 4 | 6 |
| 17 | የመጋረጃ ዘንግ (ለብቻ ሲመጣ) | በሜትር | | 16 | 10 | 16 |
| 18 | መጋረጃ ዘርፍ(ለብቻ ሲመጣ) | በሜትር | | 50 | 50 | 60 |
| 19 | የተዘጋጀ የሶፋ ጨርቅ | በቁጥር | | 12 | 16 | 24 |
| 20 | የአበባ ማስቀመጫ ፖት(ቫዝ) | ቁጥር | | 6 | 8 | 12 |
| 21 | የተለያዩ ምስል የተቀረፀበት ቅርፃ ቅርፅ ከመፅድን ወጪት ባስተቀር | ቁጥር | 2 | 3 | 3 | 4 |
| 22 | የጠረጴዛ ቬንት ሌተር(ፋን) | ቁጥር | | 2 | 1 | 2 |
| 23 | ግድግዳ ላይ የሚሆን ኤይር ኮንዲሽነር(ቬንት ሌተር) | ቁጥር | | 2 | 4 | 4 |
| 24 | የቤትውስጥማሞቂያ(Heater)እስከ 1000wat | ቁጥር | | 1 | 2 | 2 |
| 25 | የገና ዛፍ ወይም የአበባ ዛፍ | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 |
| 26 | የፎቶ ፍሬም(ከ20-40ሳ.ሜ) | ቁጥር | 2 | 12 | 12 | 12 |
| ተ.ቁ | 15 የስፖርት ዕቃዎች | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት |
| 1 | የአዋቂ ብስክሌት | በቁጥር | | 1 | 2 | 2 |
| 2 | የልጅ ብስክሌት | በቁጥር | 1 | 2 | 2 | 3 |
| 3 | የቤት ውስጥ የጂምናዚየም ማገኛውም አይነት | በቁጥር | | 2 | 1 | 2 |

Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት |
| 8 | ጀልባ እስከ 5ሠው መያዝ የሚችል | በቁጥር | | 1 | | 1 |
| ተ.ቁ | 17 ምግብና መጠጦች | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት |
| 1 | ማስቲካ ፣ቸኮሌት ወዘተ | በኪሎ | 2 | 6 | 4 | 12 |
| 2 | ማንኛውም የታሸገ የምግብ አይነት | ኪሎ | 5 | 10 | 10 | 20 |
| 3 | ማንኛውም ከአልኮል ውጪ ያለ መጠጥ | በደርዘን | 2 | 4 | 4 | 6 |
| 4 | ወይን እና ሌሎች የአልኮል መጠጦች | ሊትር | 2 | 6 | 6 | 6 |
| 5 | ሌሎች የተለያዩ የአልኮል መጠጦቸ | ሊትር | 2 | 4 | 2 | 4 |
| ተ/ቁ | 18. ኮስሞቲክስ | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው |
| 1 | የተለያዩ ቅባቶች | በደርዘን | 1 | 2 | 2 | 4 |
| 2 | ሽቶ | ሚሊ. ሊትር | 600 | 1200 | 1200 | 2400 |
| 3 | የተለያዩ የውበት መጠበቂያ | በደርዘን | 1 | 2 | 2 | 4 |



Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት |
| 1 | በሀኪም ትዕዛዝ ለግል ጥቅም የሚመጣ መድሀኒት | ቁጥር | ነፃ | ነፃ | ነፃ | ነፃ |
| 2 | ያለ ሀኪም ትእዛዝ የሚወሰድ እንደ ቫይታሚን (vitamin) ፣ food suplement | ቁጥር | ነፃ | ነፃ | ነፃ | ነፃ |
| ተ/ቁ | 22. የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት |
| 1 | የግል ህክምና የስኳር ህመም መለኪያ | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 2 |
| 2 | የግል ህክምና የደም ግፊት መለኪያ | ቁጥር | 1 | 1 | 2 | 2 |
| 3 | ማሳጅ መሳሪያዎች ትናንሽ | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 4 | የሲራጅም መሳሪያዎች | ቁጥር | | 1 | | 1 |
| 5 | የቦርጭ ማጥፊያ ቀበቶ | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 2 |
| 6 | ሌሎች አነስተኛ መጠን ያላቸው በእጅ የሚያዙ ለግል ህክምና መጠቀሚያ የህክምና | ቁጥር | 1 | 1 | 3 | 4 |
| ተ/ቁ | 23. ለእምነት አገልግሎት የሚውሉ | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት |
| 1 | የእምነት መፅሀፎችና ተያያዥ የህትመት ውጤቶች የተለያየ አይነት(ከእምነት ተቋማት ማረጋገጫ ሲቀርብ) | በቁጥር | ነፃ | ነፃ | ነፃ | ነፃ |

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት |
| ተ/ቁ | **24. ትምባሆ** | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና |
| 1 | የተለያየ ዓይነት ሲጋራዎች | እስቴካ | 1 | 2 | 2 | 4 |
| 2 | ትምባሆ | ግራም | 250 | 500 | 250 | 500 |
| ተ/ቁ | **25. ልዩ ልዩ ገቢ ዕቃዎች** | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ እቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ብዛት |
| 1 | የሴራሚክ ጠፍጣፋ ሸክላዎች | ካሬ .ሜ | | 100 | | 100 |
| 2 | የስልክ መዝጊያ(telephone Lock) | ቁጥር | | 3 | 4 | 8 |
| 3 | የተለያዩ መፍቻ (ሀንድ ቱልስ) አነስተኛ የሚካኒክ/የአናጢ ዕቃዎች ሜትር፣ውሃ ልክ ጨምሮ ከየአይነቱ | ሴት | | 1 | 1 | 4 |
| 4 | የልብስ ስፌት መኪና ከነ አክሰሳሪው (ኢንዱስትሪያል ታይፕ ያልሆነ) | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 |
| 5 | የቢሮ ተሽከርካሪ ወንበር | ቁጥር | | 2 | 2 | 2 |
| 6 | የእጅ ሰዓት | ቁጥር | 2 | 6 | 4 | 6 |
| 7 | መነፅር | ቁጥር | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 8 | ሲዲ ፕሌየር(ዲስፕለይ)የሚያገለግል የሰው ምስል የሚያሳይ | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 |

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | |
| 9 | የተለያዩ ዕቀዎች ማሳይ የሚያውል ዲስፕሌይ | ቁጥር | | 1 | | 1 | |
| 10 | የአታክልት ውሀ ማጠጫ ላስቲክ | ሜትር | | 50 | 20 | 50 | |
| 11 | የበር እጀታ | ቁጥር | | 5 | | 10 | |
| 12 | የበር ተለጣፊ ቁልፎች | ቁጥር | | 5 | 8 | 10 | |
| 13 | የበር ተንጠልጣይ ቁልፎች | ቁጥር | | 5 | 8 | 10 | |
| 14 | ቀለም | ጋሎን | | 4 | 4 | 8 | |
| 15 | የዕቃ ማመላለሻ ጋሪ | ቁጥር | | 1 | 1 | 2 | |
| 16 | ጂፕሰም ሞልድ (የግድግዳ ላይ ጌጣጌጥ | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| 17 | እስከ 50 ኪ/ግ የሚያመዝን አነስተኛ የብር ካዝና | ቁጥር | | 1 | 1 | 2 | |
| 18 | አየር ማስወጫ ሽታ መከላከያ (ፋን) | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| 19 | አነስተኛ ዌልዲንግ(መበየጃ) ማሽን | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| 20 | አነስተኛ ኤልክትሮኒክስ ዕቃ መበየጃ (ሶልደሪንግ) | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| 21 | የተለያዩ አርተፊሻል ጌጣጌጦች | ሴት | 2 | 6 | 6 | 6 | |
| 22 | ፌስታል | ደርዘን | በግል መገልገያ ዕቃነት መግባት የለበትም | | | | |
| 23 | የሰርገኞቹ ስም የታተመበት የሰርግ ካርድ | ቁጥር | ነፃ | | ነፃ | | |
| 24 | ያልታተም የሰርግ ጥሪ ካርድ | ቁጥር | | 1000 | 500 | 1000 | |
| 25 | መንሸራተቻ | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| 26 | የዕቃ ሚዛን እስከ 10 ኪ/ግ የሚመዝን | ቁጥር | | 2 | 1 | 2 | |
| 27 | የሰው ሚዛን | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |

የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2
Revenues and Customs Au...
...ords & Documentation No.

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | |
| 28 | የተለያዩ መጽሐፍት | ቁጥር | ነፃ | ነፃ | ነፃ | ነፃ | |
| 29 | አነስተኛ የሳር ማጨጃ መኪና | ቁጥር | | 1 | | 1 | |
| 30 | በፀሀይ ብርሃን የሚሰራ መብራት (Black Solar Bollard Light) | ቁጥር | 2 | 2 | 2 | 4 | |
| 31 | ባዶ ሳጥን | ቁጥር | | 2 | 1 | 3 | |
| 32 | የአቅጣጫ መጠቆሚያ (compass) | ቁጥር | 1 | 2 | 2 | 3 | |
| 33 | የፕላስቲክ ገመድ | ቁጥር | 20 | 10 | 30 | 10 | |
| 34 | የእጅ ባትሪ(ማንኛውም ዓይነት) | ቁጥር | 2 | 4 | 4 | 6 | |
| 35 | የባትሪ ድንጋይ | ቁጥር | 15 | 15 | 15 | 15 | |
| 36 | ኩለር | ቁጥር | | 1 | 1 | 2 | |
| 37 | ባይናኩላር (ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው በትልቅ ባትሪ የሚሰራ ከሆነ የተጓዳኝ መ/ቤት ፍቃድ | ቁጥር | እንደ ግል መገልገያ የማይቆጠር | | | | |
| 38 | ቴሌስኮፕ | ቁጥር | | 1 | | 2 | |
| 39 | የፎቶ ፊልሞች | ቁጥር | 5 | 10 | 5 | 10 | |
| 40 | አነስተኛ የበረዶ መስሪያ (ፕላስቲክ ወይም | ቁጥር | 1 | 2 | 2 | 2 | |
| 41 | ሉል | ቁጥር | | 2 | 2 | 2 | |
| 42 | መጥሪያ ደወል | ቁጥር | 1 | 2 | 2 | 2 | |
| 43 | የመኪና አላርም | ቁጥር | | 1 | | 1 | |
| 44 | ፋኖስ | ቁጥር | 2 | 4 | 2 | 4 | |
| 45 | ማሾ | ቁጥር | 2 | 4 | 2 | 4 | |
| 46 | የውሃ ማጣሪያ(Water Dispenser) | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 47 | ድሪል አነስተኛ | ሴት | | 1 | 1 | 1 | |

| | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ | ረ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የሚፈቀድ የግል መገልገያ ዕቃዎች ብዛት | ለንግድ አላማ የማይውሉ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት | |
| 48 | አነስተኛ ለቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውል የእንጨት መላጊያ | ቁጥር | | 1 | 1 | 2 | |
| 49 | አነስተኛ ለቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውል የእንጨት ማለስለሻ | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| 50 | ጀነሬተር እስከ 8 ኪሎ wat | ቁጥር | | 1 | 1 | 1 | |
| | **26. ወጪ የግል መገልገያ ዕቃዎች ዝርዝር** | | | | | | |
| 1 | ሽሮ | በኪሎ | 20 | | | | |
| 2 | በርበሬ | በኪሎ | 20 | | | | |
| 3 | ክክ፣ | በኪሎ ግራም | 20 | | | | |
| 4 | ድፍን ምስር፣ አተር፣ ባቄላ፣ ሽምቡራ፣ ቦሎቄ ወዘተ (ከእያንዳንዱ) | በኪሎ ግራም | 20 | | | | |
| 5 | ሽንኩርት | በኪሎ | 20 | | | | |
| 6 | ዱቄት ( ማንኛውም ዓይነት) | በኪሎ | 30 | | | | |
| 7 | ቆሎ፣ ዳቦቆሎ | በኪሎ | 20 | | | | |
| 8 | የተቆላ ቡና | በኪሎ | 10 | | | | |
| 9 | የተፈጨ ቡና | በኪሎ | 10 | | | | |
| 10 | ጥሬ ቡና | በኪሎ | 10 | | | | |
| 11 | ቅመማቅመም | በኪሎ ግራም | 10 | | | | |
| 12 | ሌሎች | በኪሎ ግራም | 20 | | | | |

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2